የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፺፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 92
ADDIS ABABA, 27th July, 2016

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፸/፪ሺ፰ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር (ማሻሻያ) አዋጅ......................................ገፅ ፱ሺ፩፻፷፯

**CONTENTS**

Proclamation No. 970/2016

Federal Government of Ethiopia Financial Administration(Amendment) Proclamation...page 9167

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፸/፪ሺ፰

## የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፱፻፸/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ማሻሻያ**

የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጾች (፲፩)፣ (፲፪)፣ (፲፫)፣ (፲፬)፣ (፲፰) እና (፳፫) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፲፩)፣ (፲፪)፣ (፲፫)፣ (፲፬)፣ (፲፰) እና (፳፫) ተተክተዋል፤

## PROCLAMATION No.970/2016

## A PROCLAMATION TO AMEND THE FEDERAL GOVERNMENT OF ETHIOPIAN FINANCIAL ADMINISTRATION PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Federal Government Ethiopian Financial Administration Proclamation;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Federal Government of Ethiopia Financial Administration (Amendment) Proclamation No.970/2016".

**2. Amendment**

The Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No.648/2010 is hereby amended as follows:

1/ Sub-articles (11), (12), (13), (14), (18) and (23) of Article 2 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (11), (12), (13), (14), (18) and (23):

"፲፩/ 'የችሮታ ጊዜ' ማለት ባለፈው የበጀት ዓመት ከተከናወነ ፕሮግራም፣ ንዑስ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ የቀረበው የካፒታል ክፍያ ጥያቄ ካለፈው ዓመት የፕሮግራሙ ፣የንዑስ ፕሮግራሙ ወይም የፕሮጀክቱ በጀት ላይ የሚከፈልበት ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ ያለው ፴ ቀናት ጊዜ ነው፤

፲፪/ 'ተጨማሪ በጀት' ማለት በበጀት ዓመቱ ለመንግሥት ሥራዎች ማስፈጸሚያ ከፀደቀው የገቢ በጀት በላይ ለመሰብሰብ ወይም የወጪ በጀት ያልፀደቀለት የመንግሥት ሥራ በማጋጠሙ ወይም የፀደቀው የወጪ በጀት በቂ ባለመሆኑ ምክንያት የሚፀድቅ ተጨማሪ በጀት ነው፤

፲፫/ 'ሚኒስቴር' ወይም 'ሚኒስትር' ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፬/ 'ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦች' ማለት ከታክስ እና በታክስ ላይ ከተጣለ ወለድ ወይም መቀጫ በስተቀር ለፌደራል መንግሥት ሊከፈል የሚገባ ማናቸውም ገንዘብ ነው፤

፲፰/ 'ምህረት' ማለት ታክስን፣ በታክስ ላይ የተጣለን ወለድና መቀጫ ወይም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦችን መማር ወይም ነጻ ማድረግ ነው፤

፳፫/ 'የበጀት ዝውውር' ማለት ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚያስተዳድሯቸው ፕሮግራሞች፣ ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች ወይም የመደበኛ ወጪ ዋና ዋና ተግባራት መካከል እና በእነዚህ ውስጥ በሂሳብ መደብ ደረጃ እንዲሁም ከመጠባበቂያ በጀት ላይ የሚደረግ

"11/ 'grace period' means the thirty days period commencing on Hamle 1 of the Ethiopian Calendar during which invoices received for capital activities of a program, sub-program or project carried out in the previous fiscal year may be paid from the previous fiscal year's capital budget of the program, sub-program or project;

12/ 'supplementary budget' means budget approved to collect additional revenue beyond the revenue already approved for activities of the Government to be carried out in a fiscal year or in situations where budget is required for an activity of the Government to which expenditure budget is not approved or where the expenditure budget approved for an activity is not sufficient;

13/ 'Ministry' or 'Minister' means the Ministry or the Minister of Finance and Economic Cooperation respectively;

14/ 'other receivables' means any amount owing to the Federal Government other than tax or interest or penalty on tax;

18/ 'remission' means the discharge or release from taxes, interests and penalties on taxes or other receivables;

23/ 'budget transfer' means an authorized transfer of budget from one public body to another public body, between and among programs, sub-programs, projects or main activities of recurrent expenditure administered by public bodies as well as from contingency budget;"

የተፈቀደ የበጀት ዝውውር ነው፤”

፪/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፴፩) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፴፪) እና (፴፫) ተጨምረው ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፴፪) ንዑስ አንቀጽ (፴፬) ሆኖ ተሸጋሽጓል፤

“፴፪/ 'ታክስ' ማለት ለዚህ አዋጅ ዓላማ ማናቸውንም በፌደራል መንግሥት ሕግ የተጣለ ወይም የሚጣል ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ግብር እና ታክስ ነው፤

“፴፫/ 'የፋይናንስ አስተዳደር የሥራ ክፍሎች' ማለት የበጀት፣ የክፍያ፣ የሂሳብ፣ የግዥ፣ የንብረት አስተዳደር እና የኦዲት ተግባራትን የሚያከናውኑ የሥራ ክፍሎች ናቸው፤”

፫/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሮ፤ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (፫) እስከ (፲፪) ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

“፪/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ያለውን የፋይናንስ አስተዳደር የሥራ ክፍሎችን አደረጃጀት ከሚመለከተው የመንግሥት አካል እና ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ይወስናል፤”

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) (እንደተሸጋሸገው) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፤

“፫/ በፌደራል እና በክልል መንግሥታት መካከል የሚደረገውን የፋይናንስ ግንኙነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ተጣጥመው ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤”

2/ The following new sub-articles (32) and (33) are added after sub-article (31) of Article 2 of the Proclamation and the existing subsequent sub-article (32) is re-numbered as sub-article (34):

“32/ 'tax' means, for the purpose of this Proclamation, any direct or indirect tax levied or to be levied by the law of the Federal Government;

33/ 'financial administration departments' mean the departments which undertake the functions of budget, disbursement, accounting, procurement, property administration and audit;”

3/ The following new sub-article (2) is added following sub-article (1) of Article 5 of the Proclamation and the existing subsequent sub-articles are re-numbered as from sub-article (3) up to (12), respectively:

“2/ decide on the organization of the financial administration departments within public bodies, in consultation with the concerned public body and the Ministry of Public Service and Human Resource Development;”

4/ Sub-article (3) of Article 5 of the Proclamation (as re-numbered) is deleted and replaced by the following new sub-article (3):

“3/ lead, coordinate and ensure harmonization of the financial relations between the Federal and Regional Governments;”

፭/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፲፪) (እንደተሸጋሸገው) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፫) ተጨምሯል፤

"፲፫/ እንደአስፈላጊነቱ ለየመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በተናጠል ወይም ለተወሰኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጋራ የውስጥ ኦዲትን ተግባር የሚያግዝ ገለልተኛ የኦዲት ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡"

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ለ) ተተክቷል፤

"(ለ) የውስጥ ኦዲት በነጻነት፣ ውጤታማ፣ ፈጣንና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ መከናወኑን ያረጋግጣል፤"

፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፯ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተጨምሮ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች (፩) እና (፪) እንደቅደምተከተላቸው ንዑስ አንቀጾች (፪)እና (፫) ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

"፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የውስጥ ኦዲት ኃላፊ እና ባለሙያዎች ተጠሪነት ለሚኒስትሩ ይሆናል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡"

፰/ በአዋጁ አንቀጽ ፲ ከንዑስ አንቀጽ (፫) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፬) እና (፭) ተጨምረዋል፤

"፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ቢኖርም ሚኒስትሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቱን የተለየ የሥራ ባሕሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚሰበስበው የውስጥ ገቢ እንዲጠቀም ሊፈቅድ ይችላል፤ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው በመመሪያ ይወሰናል፡፡



5/ The following new sub-article (13) is added following sub-article (12) of Article 5 (as re-numbered) of the Proclamation:

"13/ setup an independent audit committee either for each public body separately or for group of public bodies, as the context requires, which supports the functions of internal audits."

6/ Paragraph (b) of sub-article (2) of Article 6 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new paragraph (b):

"b) ensuring that the internal audits are carried out independently, efficiently, effectively and economically;"

7/ The following new sub-article (1) is added under Article 7 of the Proclamation and the existing subsequent sub-articles (1) and (2) are re-numbered as sub-article (2) and (3), respectively:

"1/ The head and professional staffs of internal audits of public bodies shall be accountable to the Minister. The details shall be determined by a directive to be issued by the Ministry."

8/ The following new sub-articles (4) and (5) are added following sub-article (3) of Article 10 of the Proclamation:

"4/ The Minister may allow a public body to expend internally collected revenue taking into consideration the special nature of the work of the public body; the details of which shall be provided by the directive of the Ministry.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ሥራ ላይ የዋለው የገንዘብ መጠን በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በግልጽ ተለይቶ መመልከት አለበት።"

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀፅ (፪) እና (፫) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፪)፣ (፫) እና (፬) ተተክተዋል፤

"፪/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከሚኒስትሩ በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት ከማንኛውም ታክስ፣ በታክስ ላይ ከሚከፈል ወለድና መቀጫ ምህረት ሊያደርግ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ቢኖርም ሚኒስትሩ በቂ ምክንያት ሲኖረው በታክስ ላይ ከተከፈለ ወይም ከሚከፈል ወለድ ምህረት ሊያደርግ ይችላል።

፬/ ሚኒስትሩ በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እስከተወሰነው የገንዘብ መጠን ድረስ ከታክስ ወይም ሌሎች ተሰብሳቢዎች ዕዳ ምህረት ሊያደርግ ይችላል።"

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ተተክተዋል፤

"፩/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፫ በተደነገገው መሠረት የሚደረግ ምህረት በሙሉ ወይም በከፊል፣ በገደብ ወይም ያለገደብ ሆኖ፣

5/ The amount of money utilized in accordance with sub-article (4) of this Article shall be shown in the financial report of the public body."

9/ Sub-articles (2) and (3) of Article 13 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (2), (3) and (4):

"2/ The Council of Ministers may, for good cause and upon the recommendation of the Minister, remit from any tax, interest and penalty on tax.

3/ Notwithstanding to the provision of sub-article (2) of this Article, the Minister may for good cause remit from an interest paid or to be paid on tax.

4/ The Minister may for good cause remit any tax or other receivable up to an amount determined by a Regulation issued by the Council of Ministers."

10/ Sub-articles (1) and (2) of Article 14 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (1) and (2):

"1/ A remission of the types provided under Article 13 of this Proclamation may be total or partial or conditional or unconditional and may be granted:

ሀ) ታክስ፣ በታክስ ላይ ከሚከፈል ወለድና መቀጫ ወይም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ለማስገባት ጉዳዩ ለክስ ከተመራ፣ ክሱ ከተጀመረ ወይም ከመጀመሩ በፊት፤

ለ) ታክስ፣ በታክስ ላይ ከሚከፈል ወለድና መቀጫ ወይም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦች በፍርድ አፈጻጸም ከመከፈላቸው በፊት ወይም ከተከፈሉ በኋላ፤

ሐ) ታክስን ወይም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦችን የሚመለከት ማናቸውም ጉዳይ ወይም ጉዳዮች ሲኖሩና የመክፈል ኃላፊነትን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ከመድረሳቸው በፊት ሊሰጥ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ምህረት የተደረገው በተከፈለ ታክስ ላይ ሲሆን፣ ምህረት የተደረገው ገንዘብ መጠን ታክስ ከፋዩ ለወደፊት ከሚከፍለው ታክስ ላይ እንዲካካስ ይደረጋል።"

፲፩/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፤

"፫/ የመንግሥት በጀት ዝግጅት ሥርዓተ ጾታን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።"

፲፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤

a) before, after or pending any suit for the recovery of the tax, interest and penalty on tax or other receivable in respect of which the remission is granted;

b) before, or after any payment of the tax, interest and penalty on tax or other receivable has been made or enforced by process or execution;

c) with respect to a tax or other receivable in any particular case or class of cases and before the liability for it arises.

2/ Where a remission granted in accordance with this Article is on tax paid, the amount of tax remitted shall be set off against the tax payable by the payer in future tax years."

11/ The following new sub-article (3) is added following sub-article (2) of Article 20 of the Proclamation:

"3/ Gender issues shall be taken into consideration during public budget preparation."

12/ Sub-article (1) of Article 24 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"፩/ ሚኒስትሩ፣

ሀ) በአንድ የመንግስት መሥሪያ. ቤት ውስጥ በጀትን ከአንድ ፕሮግራም ወደ ሌላ ፕሮግራም፣ ከአንድ ንዑስ ፕሮግራም ወደ ሌላ ንዑስ ፕሮግራም፣ ከአንድ ፕሮጀክት ወደ ሌላ ፕሮጀክት ወይም ከአንድ የመደበኛ ወጪ ዋና ዋና ተግባራት ወደ ሌላ ለማዘዋወር፣

ለ) በአንድ ፕሮግራም ወይም ንዑስ ፕሮግራም ውስጥ ካሉ የወጪ መደቦች በጀት ከአንዱ ወደ ሌላ ለማዘዋወር፣

ሐ) አስቀድሞ ባሉት ዓመታት ለፀደቀ እና በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተያዘለት የፕሮግራም፣ የንዑስ ፕሮግራም ወይም የፕሮጀክት ካፒታል ወጪ ቀሪ ግዴታዎች ማስፈጸሚያ የሚውል በጀት ለአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቱ ከፀደቀ የፕሮግራም፣ የንዑስ ፕሮግራም ወይም የፕሮጀክት በጀት ለማዘዋወር፤

መ) በአንድ የመንግስት መሥሪያ ቤት ሥር ያሉ ፕሮግራሞች ሲዋሃዱ ወይም ሲነጣጠሉ ለተፈጠረ ፕሮግራም በጀቱን ለማዘዋወር፤

ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡"

፲፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፭ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፭ ተተክቷል፤

"፳፭. <u>በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መካከል የሚደረግ የበጀት ዝውውር</u>

ሚኒስትሩ በሚከተሉት ምክንያቶች የአንድ የመንግስት መሥሪያ ቤት በጀት ወደሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት በጀት እንዲዘዋወር ሊፈቅድ ይችላል፤

፩/ በአንድ የመንግስት መሥሪያ ቤት ውስጥ ያጋጠመን የበጀት እጥረት ለማቃለል በበጀት ዓመቱ ለሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት የፀደቀ እና

"1/The Minister is hereby empowered to:

a) transfer budget from one program to another program, from a sub-program to another sub-program, from a project to another project or main activities of recurrent expenditure to another recurrent expenditure within a public body;

b) transfer budget between items of expenditure within a program or sub-program;

d) transfer the budget approved for a program, sub program or project of the public body to finance pending obligations pertaining to capital expenditure of a program, sub program or project approved in previous years for which no budget is allocated in the current fiscal year;

e) transfer budget to a program created where programs under a public body merge or split."

13/ Article 25 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 25:

25. **<u>Budget Transfers between Public Bodies</u>**

"The Minister may authorize the transfer of budget from one public body to another public body under the following conditions:

1/ where it is necessary to transfer unspent budget approved for one public body for that fiscal year to meet shortfall in another public body's budget, provided that such

ጥቅም ላይ ያልዋለን በጀት በማዘዋወር መጠቀም አስፈላጊ ሲሆንና ይህም ተጨማሪ በጀት ያስፈለገው ቀደም ሲል ለፀደቀ ፕሮግራም፣ ንዑስ ፕሮግራም፣ ፕሮጀክት ወይም የመደበኛ ወጪ ዋና ዋና ተግባራት መሆኑ ሲረጋገጥ፤

፪/ አስቀድሞ ባሉት ዓመታት ለፀደቀ እና በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተያዘለት ፕሮግራም፣ ንዑስ ፕሮግራም፣ ፕሮጀክት ወይም የመደበኛ ወጪ ዋና ዋና ተግባራት ቀሪ ግዴታዎች ማስፈጸሚያዎች የሚውል በጀት ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ፤

፫/ በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሥር ያሉ ፕሮግራሞች ሲዋሀዱ ወይም ሲነጣጠሉና በጀቱ ከአንዱ ወደሌላ እንዲዘዋወር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ::"

፲፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፰ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፰ ተተክቷል፤

"፳፰. __የበጀት መጽደቅ መዘግየት__

፩/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እስከ አዲሱ የበጀት ዓመት መጀመሪያ የዓመቱን በጀት ሳያፀድቀው ቢዘገይ፣ ምክር ቤቱ የዓመቱን በጀት እስከሚያፀድቀው ድረስ፣ ቀደም ሲል ለተፈቀዱ ፕሮግራሞች፣ ንዑስ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና የመደበኛ ወጪ ዋና ዋና ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ በሚኒስትሩ እየተፈቀደ ጥቅም ላይ ይውላል::

additional budget is needed for a previously approved program, sub-program, project or main activities of recurrent expenditure.

2/ where a budget is requested to finance pending obligations of a program, sub-program, project or main activities of recurrent expenditures approved in previous years for which no budget is allocated in the current fiscal year.

3/ where it is necessary to transfer a budget from one public body to the other due to merge or split of programs of a public body."

14/ Article 28 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 28:

"28. __Delay in Budget Approval__

1/ If the House of Peoples' Representatives has not approved the annual budget until the beginning of the new fiscal year, budgets for previously approved programs, sub programs, projects or main activities of recurrent expenditure shall be utilized by the approval of the Minister until the annual budget is approved by the House.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተላለፈው ገንዘብ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሚጸድቀው የዓመቱ በጀት ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።"

፲፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፬ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፬ ተተክቷል፤

"፴፬. <u>ለካፒታል በጀት የሚሰጥ የችሮታ ጊዜ</u>

በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከተከናወነ ፕሮግራም፣ ንዑስ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ የቀረበ የፕሮግራሙ፣ የንዑስ ፕሮግራሙ ወይም የፕሮጀክቱ የካፒታል ወጪ ክፍያ ጥያቄ የበጀት ዓመቱ ካለቀ በኋላ ባለው ፴ቀን ጊዜ ውስጥ ከተጠናቀቀው ዓመት የፕሮግራሙ፣ የንዑስ ፕሮግራሙ ወይም የፕሮጀክቱ የካፒታል በጀት ላይ ታስቦ ሊከፈል ይችላል።"

፲፮/ ከአዋጁ አንቀጽ ፵ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፩ ተጨምሮ፣ ከአንቀጽ ፵፩ እስከ አንቀጽ ፸፱ ያሉት ነባር አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፵፪ እስከ አንቀጽ ፹ ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

"፵፩.<u>የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ</u>

፩/ ሚኒስትሩ ተፈላጊውን የገንዘብ መጠን በተገቢው ጊዜ የመበደርን አጠቃላይ ዓላማ መሠረት ያደረገ እና ወጪ መቀነስን ከተረጋጋ ወጪ ጋር ባመዛዘነ አፈጻጸም ለመምራት እንዲሁም ብድር የዕዳ ጫና ሁኔታን እና የመክፈል አቅምን መሠረት ባደረገ አካኋን መውሰድ የሚያስችል የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ማዘጋጀት አለበት።

2/ The amount disbursed pursuant to sub-article (1) of this Article shall be deducted from the annual budget to be approved by the House of peoples' Representatives."

15/ Article 34 of the Proclamation is deleted and is replaced by the following new Article 34:

"34.<u>**Grace Period for Capital Budget**</u>

Payments of invoices in connection with capital expenditure of a program, sub-program or project carried out in a fiscal year may be made in the 30 days period following the end of the fiscal year on the account of the capital budget of the program, sub-program or project of the preceding fiscal year."

16/ The following new Article 41 is added following Article 40 of the Proclamation and the existing subsequent Articles from 41 up to Article 79 are re-numbered as Article 42 up to 80, respectively:

"41.<u>**Debt Management Strategy**</u>

1/ Debt management strategies shall be developed by the Minister based on the overall objective of borrowing appropriate amounts at appropriate times and in a way that balance minimization of cost with stability and taking into consideration the level of debt and the ability to repay.

፪/ ብድር በሚወሰድበት ጊዜ ከወለድ ውጪ የሆኑ የተለያዩ ከብድሩ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ የዚህ ዓይነቶቹ ወጪዎች የተለያዩ ኮሚሽኖችን፣ ክፍያዎችን፣ የሬጅስትራሮች እና የፋይናንስ ወኪሎች የአስተዳደር ወጪዎችን ይጨምራሉ፡፡

፫/ ብድር በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ የሆነ ውጤት በሚያስከትሉ በተለይም በገንዘብ ፖሊሲ ወይም በክፍያ ሚዛን ላይ የሚፈጠር አለመረጋጋትን የመሳሰሉ ሁኔታዎችን መከላከል በሚያስችል መንገድ መተዳደር ይኖርበታል፡፡

፬/ የአጭር ጊዜ ብድር መንግሥት በባንኮች እና በልውውጥ ገበያ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን የሂሳብ ሚዛን እንዲሁም የገቢ እና የወጪ በጀትን ግምት በሚመለከት አስተማማኝ የሆነ ወቅታዊ መረጃን መሠረት በማድረግ መፈጸም አለበት፡፡"

፲፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፰ (እንደተሸጋሸገው) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፰ ተተክቷል፤

"፵፰. ማቻቻል

፩/ በታክስ ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለመንግሥት ገቢ መደረግ ያለበትን ገንዘብ ከመንግሥት ይፈለጋል ለሚባል ተከፋይ ሂሳብ ማቻቻያ ማድረግ፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ሚኒስትሩ መንግሥት ከተበዳሪዎች የሚፈልገውን ገንዘብ ለእነዚህ ተበዳሪዎች መንግሥት ሊከፍል ከሚገባው የተረጋገጠ ዕዳ ጋር እንዲቻቻል ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2/ Borrowing shall take into account non-interest costs, such as the different marketing costs which are incidental to borrowing. These include the various commissions, fees and other administrative costs of registers and fiscal agents.

3/ Debt shall be managed in such a manner as to prevent any negative impacts on the general economy, such as creating instability in monetary policy or balance of payments.

4/ Short-term borrowing shall be based upon reliable current information on the government's balance in the banking system, exchange market activity, and budget estimates of fiscal inflows and outflows."

17/ Article 48 of the Proclamation (as re-numbered) is deleted and replaced by the following new Article 48:

"48. Set-Off

1/ Without prejudice to the relevant provisions of the tax laws, Public Money due to the Federal Government shall not be set-off against an amount claimed from the Government.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, the Minister may set-off the debt owed by creditors to the Government against confirmed debt owed by the Government to such creditors.

፫/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚቻቻለው የገንዘብ መጠን በመንግሥት የሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በግልጽ ተለይቶ መመልከት አለበት።”

፲፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፶ (እንደተሸጋሸገው) ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤

“፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከሚያወጣው ደንብ ጋር የማይቃረን እስከሆነ ድረስ ሚኒስትሩ ለግዴታ መፈጸም ዋስትና ሊሰጥ ይችላል።”

፲፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፶፯ (እንደተሸጋሸገው) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፶፯ ተተክቷል፤

“፶፯. ወደካፒታል ስለመለወጥ

ሚኒስትሩ የፌደራል መንግሥት ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚፈልገውን ዕዳ ወደ ካፒታል ለመለወጥ ይችላል።”

፳/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፸ (እንደተሸጋሸገው) ቀጥሎ አዲስ አንቀጾች ፸፩፣ ፸፪ እና ፸፫ ተጨምረው ቀጥለው ያሉት ነባር አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው እንደገና ተሸጋሽገው ከአንቀጽ ፸፬ እስከ ፹፫ ሆነዋል፤

“፸፩. የሥራ ቅንጅት

በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡት ደንብና መመሪያዎች የተዘረጋውን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ በሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት መካከል የሥራ ቅንጅት ሊኖር ይገባል።

3/ The amount set-off in accordance with sub-article (2) of this Article shall be shown in the financial report of the government.”

18/ Sub-article (1) of Article 50 (as re-numbered) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

“1/ The Minister may guarantee the performance of an obligation provided that such guarantee is in compliance with the Regulation to be issued by the Council of Ministers.”

19/ Article 57 of the Proclamation (as re-numbered) is deleted and replaced by the following new Article 57:

“57. **Conversion into Capital**

The Minister may convert debts owed to the Federal Government by public enterprises into capital.”

20/ The following new Articles 71, 72 and 73 are added following Article 70 of the Proclamation(as re-numbered); and the existing subsequent Articles are again re-numbered as Articles 74 to 83, respectively:

“71. **Co-ordination of Activities**

There shall be co-ordination of activities among the concerned public bodies to make more effective the financial administration system set by this Proclamation, the Regulation and Directives issued hereunder.”

“፸፪. **አስተዳደራዊ ቅጣቶች**

፩/በማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት በወጡት ደንብ እና መመሪያዎች መሠረት እንደሁኔታው ዕቅድ ወይም የሒሣብ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ወይም ለውጭ ኦዲተር ያላቀረበ ወይም መቅረቡን ያላረጋገጠ ወይም በውጭ ኦዲት ወይም በውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተመለከተው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ያልወሰደ ወይም እርምጃ መወሰዱን ያላረጋገጠ እንደሆነ ኃላፊነቱን በአግባቡ ባለመወጣቱ ከብር ፭ ሺ. እስከ ብር ፲ ሺ. በሚደርስ ቅጣት ይቀጣል።

፪/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚጣል አስተዳደራዊ ቅጣት በእያንዳንዱ ኃላፊነቱን በአግባቡ ባለመወጣቱ ምክንያት የሚጣል ይሆናል፤ ሆኖም በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣት ከሦስት ጊዜ በላይ አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ሰው ከኃላፊነቱ እንዲነሳ ሚኒስትሩ እንደ አግባብነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ወይም ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ጥያቄ ያቀርባል።

፫/ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ይጥላል እንዲሁም ያስፈጽማል፤ ይህንን ለማስፈፀም የሚያስችል ዝርዝር መመሪያም ያወጣል።

“፸፫. **በኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች ስለመጠቀም**

ሚኒስትሩ በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት በሚወጣው ደንብ የተዘረጋው የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ይበልጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ የኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።”

72. **Administrative Penalties**

1/ Where any person appointed to or employed by a public body, who should have but failed to submit or ensure the submission of plans or financial report to the Ministry or external auditor, failed to take corrective measures based on audit findings of internal or external audit or ensure that such measures are taken, in accordance with this Proclamation, the Regulation and Directives issued hereunder, as the case maybe, breaches duty and shall be liable to administrative penalty of Birr 5,000 to 10,000.

2/ The administrative penalty to be imposed pursuant to sub-article (1) of this Article shall be for each instance of breach of duty; provided, however, if a person has been penalized for failing to discharge his duty for more than three times the Minister shall request the Prime Minister Office or Ministry of Public Service and Human Resource Development, as the case maybe, to dismiss such person.

3/ The Minister shall impose and cause the enforcement of the administrative penalties provided for under sub-articles (1) and (2) of this Article and issue a directive for proper implementation thereof.

“73. **Using Electronic Methods**

To enhance the efficiency and effectiveness of the public finance administration system introduced by this Proclamation and the Regulation to be issued hereunder, the Minister shall promote the extensive use of electronic methods.”

**፫. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሀምሌ ፳ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**3. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of July ,2016**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**